# ለውጥ ታሪካዊ ውል

የየካቲቱ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሪቮሉሽናዊ እንቅስቃሴ ፈንድቶ በገሃድ መንበልበል በጀመረ በአመቱ፡ የፊውዳሊዝሙን ስርአት ኢኮኖሚያዊ መሰረት የሚደመስስ፡ 'መሬት ላራሹን' እውነት የሚያደርገው በስራ ላይ የሚያውል አዋጅ ወጥቶአል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝቦች በከባድ መስዋእትነት ለሚያካሂዱት ሪቮሉሽናዊ ትግል አንድ አቢይ ድል ተቀዳጅተዋል፡፡ 'መሬት ላራሹ' በሚለው የሰፊው ሕዝብ ከፍተኛ ጥሪ ስር በመሰለፍ የሃይለስላሴን ፋሺስታዊ ጭቆናና ብዝበዛ የተቋቋሙትና ህይወታቸውን ጭምር የሰዉት የኢትዮጵያ ሰማእታት ምኞት ወደ ተግባር የሚተረጎምበት በር ዛሬ ተከፍቶአል ለማለት ይቻላል፡፡ የሰማእታቱ ደም በከንቱ አልፈሰሰም፡፡ 'መሬት ላራሹን' በስራ ላይ ለማዋል የወጣው የዛሬው ታሪካዊ አዋጅ በሰማእታቱ ደም በቅሉ የአደገ ዛፍ አበባ ነው፡፡

በርግጥ በዛሬው ቀን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አዲስ ምእራፍ ተጀምሮአል፡፡ ነገር ግን የዚህን አዋጅ በትክክል በስራ ላይ መዋል የሚቃወሙ ሃይሎች አሁንም ያሉ መሆናቸው አያጠራጥርም፡፡ የመሳፍንትና መኳንንት ርዝራዦች፡ የገጠሩ ባላባታዊ መደብ፡ የቢሮና አቀባባይ ከበርቴዎች፡ እንደዚሁም የንኡስ ከበርቴው ቀኝ ክንፍ ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ተደርበው በኢትዮጵያ መሰረታዊ ለውጥ እንዳይደረግ፣ መሬቱ በርግጥም በአዋጁ መሰረት የሕዝብ እንዳይሆን ባላቸው አቅም ሁሉ ለማጨናገፍ ይሞክራሉ፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦች በርግጥ የወደፊት እድላቸውን በገዛ እጃቸው እንዳያገኙ የተቻላቸውን ያህል ይጥራሉ፡፡ አገሪቱዋ ራሱን የቻለ ነፃ ኢኮኖሚ እንዳትገነባና በጠቅላላው መሳፍንታዊ ስርአትና ኢምፔሪያሊዝም ተመልሰው በሰፊው ሕዝብ ጫንቃ ላይ የጭቆናና የዘረፋ ቀንበራቸውን እንዲጭኑ በሃይል ይታገላሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ወዛደሩ፡ ደሃውና ጢሰኛው ገበሬ፡ ተራማጅ ወታደርና ምሁር፡ በአጠቃላይ የሰፊው ሕዝብ ወገኖች አዋጁ ከስራ ላይ እንዲውል፡ ፊውዳሊዝሙ ስርአትና ኢምፔሪያሊዝም ተደምስሰው ብሄራዊው ዲሞክራሲያዊ ሪቮሉሽን ግቡን እንዲመታና ወደፊት እንዲቀጥል አጥብቀው ይታገላሉ፡፡

በቀዩ የደም ቀለም የተፃፈው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ታሪክ ውስጥ ይህ 'የመሬት ላራሹ' አዋጅ የዋናው ትግል መጀመሪያ እንጂ መደምደሚያው አይደለም፡፡ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ገና ዲሞክራሲያዊ መብቶቹንና ነፃነቶቹን መቀዳጀት አለበት፡፡ ገና እንደአንዱ ሰው ተነስቶ መሳፍንታዊውን ስርአትና ኢምፔሪያሊዝምን መደምሰስ አለበት፡፡ በነርሱም መቃብር ላይ አዲስ በወዛደሩ መደብ የሚመራ ሕዝባዊ ስርአትን መመስረት ይኖርበታል፡፡

የኢትዮጵያ ተራማጆች ሁሉ ከሰፊው ሕዝብ ጎን በመሰለፍ የዛሬውን ታሪካዊ አዋጅ ይደግፉታል፡፡ ከስራ ላይ እንዲውልም ከመቼውም ይበልጥ አንድነታቸውን አጠንክረው ይታገሉለታል፡፡ ይህንን አዋጅ ከሚደግፉና ለኢትዮጵያ ሕዝቦች እውነተኛ ነፃነት ከሚታገሉ ሃይሎች ጋራ ያላቸውን የትግል አንድነት በማጠንከር የአድሃሪያንንና የኢምፔሪያሊዝምን ሴራ እስከመጨረሻው ይቋቋሙታል፡፡

ይሁንናም፣ የተያዘው ሪቮሉሽናዊ ትግል ግቡን እንዲመታ ከተፈለገ፡ ሰፊው ሕዝብ እራሱ እንዲደራጅ የወደቀበት ገደብ ቶሎ ብሎ መነሳት ይኖርበታል፡፡ ወዛደሩ፡ ገበሬው፡ ተራማጅ የሰፊው ሕዝብ ወገንና የተጨቆኑ የሕዝብ ክፍሎች ሁሉ መደራጀትና ትግላቸውን በገዛ እራሳቸው ማካሄድ አለባቸው፡፡ የሰፊውን ሕዝብ በነፃ መደራጀትና የዲሞክራሲያዊ መብቶችን ለሰፊው ሕዝብ መመለስ የሚቃወሙና የተጀመረውን ሪቮሉሽናዊ እንቅስቃሴ ወደቢሮክራሲያዊ የለውጥ ጉዳና ለማዞር የሚፈልጉ ሁሉ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የሰፊውን ሕዝብ ድሎች የሚያደናቅፉና የትግሉንም እንቅስቃሴ የሚገቱ የለውጥ እንቅፋቶች ናቸው፡፡ ይህን ደህና አድርገው እንዲገነዘቡት ያስፈልጋል፡፡ ታጥቦ ጭቃ እንዳይሆን መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝቦች ከንግዲህ ወደኋላ ከማይመለሱበት አቢይ የትግል ምእራፍ ላይ ደርሰዋል፡፡ ሰማያት ቢናወጡ፡ መሬት ብትናዠቅ እንግዲህ መሳፍንታዊው ስርአትና ኢምፔሪያሊዝም ከስረመሰረታቸው ሳይወድሙ፡ አዲስ ሕዝባዊ ስርአት ሳይቋቋምና የኢትዮጵያ ሕዝቦች የራሳቸውን እድል በእጃቸው ሳይጨብጡ የየካቲቱ የትግል እንቅስቃሴ ከቶ ገብ አይልም፡፡ ትግሉ መራራና ከፍተኛ መስዋእትነት የሚጠይቅ፡ ብዙ ውጣ ውረድ የሚኖርበት መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ቢሆን፣ ከእንግዲህ ሰፊው ሕዝብ ወደነበረበት

የብዝበዛና የጭቆና ቀንበር ስር አይመለስም፤ እስከመጨረሻው የደሙ ጠብታ ድረስ በቆራጥነት ይዋጋል እንጂ::

ይህ ታሪካዊ አዋጅ፡ይህ የሰፊው ሕዝብ አቢይ ድል ከንቱ ሆኖ እንዳይቀር ሰፊው ሕዝብ፡ ሰፊው አፈር ገፊ ሙሉ በሙሉ እንዲሳተፍበትና እንዲደገፈው አስፈላጊ ነው::ይህም ሊሆን የሚችለው የሰፊው ሕዝብ ዴሞክራሲ፡የንግግር የጽሁፍ የድርጅት የስብሰባ ወዘተ. መብቶችና ነፃነቶች በስራ ላይ ሲውሉ ነው::ሰፊው ሕዝ'' በኢኮኖሚ በኩል የተቀዳጃቸውን ድሎች በቁጥጥሩ ስር ሊያደርጋቸው፡ እንደራሱ አድርጎ ሊሳተፍባቸው የሚችለው፡የፖለቲካ ጥያቄዎቹ የተመለሱለት፡ዴሞክራሲያዊ መብቶቹና ነፃነቶቹ በተግባር የተረጋገጡለት እንደሆነ ብቻ ነው::ትክክለኛው መንገድ ይህ ነው::ሌላ አማራጭ ከቶ የለም::

ታሪካዊው አዋጅ ስራ ላይ እንዲውል የሰፊው ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብቶች በተግባር ይረጋገጡ፤
ፊውዳሊዝም፡ኢምፔሪያሊዝም፡ፋሽዝምና ታሪካዊውን አዋጅ የሚቃወሙ አድሃሪያን ሁሉ ይውደሙ::

ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው::

ከሰፊው ሕዝብ
ድምጽ ዝግጅት
የወጣ ለዩ
መግለጫ
...
አአ.25/6/67